# በኢፌዲሪ መንግሥት ለ 2023 ዓለም አቀፍ የስደተኞች ጉባዔ (GLOBAL REFUGEE FORUM – GRF) የሚቀርቡ አዲስ ቃል-ኪዳኖች

## 01

ከፍተኛ ቁጥር ያለው ስደተኛ በማስጠለል እየተከሰተ ላለው የተፈጥሮ ሀብት ውድመት 100,000,000 ዘርፈ-ብዙ ችግኞችን በመትከል፣ የአካባቢ መልሶ ማልማት ተግባራትን በማከናወን፣ የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎችን ከብሔራዊ የኤሌክትሪክ ግሪድ ጋር በማስተሳሳርና የፀሐይ ኃይል ግሪድ በመዘርጋት ምላሽ መስጠት፤ እንዲሁም ስደተኞችን በብሄራዊ አዳፕቴሽን ዕቅድ ውስጥ ማካተት።

## 02

ተመረጡ የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎችን መንገድ፣ መብራት፣ ውኃ፣ የአካባቢ ንፅህና፣ ጤና እና ትምህርት የመሳሰሉ አገልግሎቶችንና መሠረተ ልማቶችን በማሻሻል ከአጎራባች ከተሞች ማስተር ፕላን ጋር አዋህዶ እ.አ.አ በ2027 ወደ ዘላቂና ምቹ ከተማነት ማሳደግ።

## 03

የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አቅም በማሳደግ እ.አ.አ በ2027፣ 1,000,000 ስደተኞችን የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ አገልግሎት የሚፈፅማቸው ብሄራዊ ፕሮጀክቶች፣ በብሄራዊ ፆታዊ ጥቃት መከላከል እና ምላሽ መርሃ-ግብሮች፣ 800,000 ስደተኞችን በብሄራዊ መታወቂያ ፕሮግራምና የሁለተኛ ደረጃ የስደተኛ ትምህርት እንዲሁም 30,000 ስደተኞችንና ተቀባይ ማህበረሰብን በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና በማካተት ከሰለጠኑት ውስጥ ለ70% የስራ ዕድል መፍጠር።

## 04

በስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎችና አካባቢው የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ እና ኢንቨስትመንት ለማሻሻል፣ አስቻይ ሁኔታዎችን በመፍጠር የስደተኞችና ተቀባይ ማህረሰቦችን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማጎልበት እና ምርታማነታቸውን ማሳደግ።

## 05

10,000 ሄክታር የመስኖ መሬት በሊዝ በማቅረብና የተቀናጀ የግብርና እና የእንስሳት ልማትን በመተግበር የስደተኞችና ተቀባይ ማህበረሰብ የምግብ ዋስትና እና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤ ከዕድሉ ተጠቃሚዎች 30% ስደተኞች እንዲሁም ከጠቅላላው 50% ሴቶች ይሆናሉ።

## 06

ዲጂታል መሠረተ ልማት ተደራሽነትን በማሳደግ፣ ስደተኛና ተቀባይ ማህበረሰብን የዲጂታል ኢኮኖሚ እና የኤሌክትሮኒክ አገልግሎቶች ተጠቃሚ ማድረግ እንዲሁም ለስደተኞች ደረጃውን የጠበቀ ዲጂታል የጉዞ ሠነድ ተደራሽ ማድረግ።